የሰ/መ/ቁ. 39014

ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብልዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መሰሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ዓለሙ መግራ - ቀረበ

**ተጠሪ**፡- እምነቴ እንደሻው ህንፃ ተቋራጭ - ነ/ፈጅ ግርማ ወርቁ ቀረቡ

መዝገቡን መርመረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበር ጉዳዩ የስራ ክርክር ሆኖ መጀመሪያ አመልካች ባቀረበው ክስ መነሻ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 19802 በ5/10/99 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች የስራ መሪ እንጂ ሰራተኛ አይደለም በማለት ክሱ በብይን ውድቅ ሲደረግ ይግባኝ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 57097 በሆነው ኀዳር 11 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ብይንን መሻር አመልካች የስራ መሪ ሳይሆን ሰራተኛ ነው በማለት በፍሬ ነገር ላይ ውሳኔ እንዲሰጥት በማዘዝ ለመጀመሪያ ፍ/ቤት ጉዳዩ ተመለሰ፡፡ ከዚህ በኋላ ክርክሩ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲካሄድ ሐምሌ 13/99 ዓ.ም በተፃፈ መቃወሚያ የግዛት ክልል ስልጣን የለም የሚለውን መቃወሚያ ቀርቦ ፍ/ቤቱ በማለፍ በፍሬ ነገር ላይ የስራ ውል የተቋረጠው አለአግባብ ነው የ6 ወር ካሳና የ2 ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና የየካቲት ወር ደመወዝ እዲከፈላቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት የግዛት ክልል ስልጣን የለውም ተጠሪ ዋና መ/ቤቱ አዋሳ ነው በማለት ውሳኔው በመሻሩ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 2 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው ቅሬታ፡-

የተጠሪ ቅርንጫፍ ቢሮ አዲስ አበባ ከተማ ያለ ስለመሆኑ በማረጋገጥ ግንቦት 3 ቀን 2000 ዓ.ም በወጣው ሪፖርተር ጋዜጣ ገጽ 8 የቅጥር ማስታወቂያ ላይ አድራሻ አ.አ መሆኑን የገለጸ ከመሆኑም በላይ በተመሳሳይ የስራ ክርክር በመ/ቁ. 29465 ፣37317 እና 38403 በየካ ምድብ ችሎት በመ/ቁ. 21206 በቂራ ምድብ ችሎት ጉዳዮች የታዩ መሆኑን በመግለጽ የግዛት ክልል ስልጣን የለም የተባለው ስህተት በመሆኑ ውሳኔው እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡

ይህ ችሎት የግዛት ክልል ስልጣን የለም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ የቃል ክርክር አካሄደዋል፡፡ የተጠሪ የቃል ክርክር አዲስ አበባ ያለው የእቃ ገቻ እና የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እንጅ ዋና መ/ቤቱ አዋሳ ነው በማለት ውሳኔው እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ በአጭሩ የተመዘገበው ሲሆን እኛም እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አስቀድሞ አመልካች የስራ መሪ ነው በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት ጉዳዩ አይታይም ተብሎ ክሱ በብይን ውድቅ ተደርጐ በይግኝ ታይቶ እንደገና እንዲታይ ተወስኖ ሲመለስ የአሁኑ ተጠሪ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን እንደገና ሊያይ የሚችልበት የግዛት ክልል ስልጣን የለውም ስልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ነው ጉዳዩ እንዲታይ እንዲመለስ የተደረገው በማለት

በይግባኝ እንዲታረምለት አልጠየቀም፡፡ በውሳኔው ተስማምቶ በፍሬ ጉዳይ ላይ ለመሟገት ከመለሰ በኋላ እንደገና የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር የሚያነሳበት የሕግ አግባብ የሌለ ከመሆኑም በላይ ይልቁንም የድርጅቱ ቅ/ጽ/ቤት አ/አበባ ከተማ ለም ሆቴል አካባቢ ኃይሌ ገ/ስላሴ መንገድ እንደሆነ አመልካች በቅሬታው የጠቀሰውን የተጠሪ ጠበቃ በክርክራቸው የእቃ ግዥ እና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ የተከራከረ በመሆኑ የግዛት ክልል ስልጣን የለውም በማለት የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ነው ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 63124 ግንቦት 6 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ፍ/ቤቱ የግዛት ክልል ስልጣን አለው ብለናል፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ በሕጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን ከሕግና ከማስረጃ አንፃር በማገናዘብ ተገቢውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሰረት ለከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ
4. መዝገቡን ዘግተናል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡
5. መ/ቁጥር 19802 በመጣበት ሁኔታ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ